# የገበሬው ልጅ ሞላ አስገዶም ! ከደምስ በለጠ

ከጋዜጠኛ ደምስ በለጠ

ከሳምንት በፊት ከወደ አስመራ አንዲት "ሰበር ዜና " የምትል ፤ እንደ አዋጅ  ቢጤ የሚቃጣት ዜና ተናኘች ። በዚህች ዜና ላይ አሳቤን እስከ አስመራ ድረስ ወስጄ ፤ እያንዳንዳቸውን ተጣመሩ የተባሉትን ድርጅቶች ለመቃኘት ሞከርኩ ። ይህን ሳደርግ ሁልጊዜ ሻእቢያ ከሚጎነጉናቸው ትብብር ፤ ጥምረት ውህደት ፤አሊያንስ ፤ እየተባሉ ከተፈለፈሉ ያለፉ ታሪኮች በመነሳት ነው ። ይህ አይነት ጥምረት ፤ ሊቋቋም እንደሚችልም በቀደሙት ፅሁፎቼ እንደ ትንቢት አድርጌ ገልጬም ነበር ። በዚህኛው ጥምረት ወይም ንቅናቄ ፤ ሻእቢያ የፈጠራ ጥበቡን በጥቂቱም ቢሆን ለማሻሻል የሞከረ ይመስላል ።

ጥምረቶቹ ውስጥ ይካተታሉ ብዬ ገምቻቸው ከነበሩት ድርጅቶች ውስጥ የደቡብ ህዝቦችንና የቤኒሻንጉል ድርጅቶችን ለጊዜው አላካተታቸውም ። "አገር አድን ንቅናቄ" የተባለው እንከን ባይገጥመው ኖሮ ፤ እነዚህ ድርጅቶች ፤ ወደፊት አገር አድን ንቅናቄውን ለማጠናከሪያ የሚመዘዙ ፤  የሻእቢያ የፖለቲካ  ጆከር  ካርታዎች ነበሩ ። ለዛሬው ግን ከአማራ ንቅናቄ እስከ አፋሮች ህብረት የዘለቀ ንቅናቄ የተባሉ ቡድኖችን ከቶበታል ። አዲስ ድርጅት መጣ ፤ ወይም ቀድሞ የነበረው ዘለቀ ፤ ዘፈኑ ሁሉ ሻእቢያ ዘንድ ያው ሽሙናዬ ነው ። ድርጅቶቹን ጉልቻዎች አድርገን ብንወስዳቸው ፤ የሾርባው ቀማሚና ፤ አድራጊ ፈጣሪ ግን ሻእቢያ  እንደሆነ  ከልምድ  ያየነው ነው ።

ከሰበር ዜናዋ ላይ ተነስቼ ይህን እያሰብኩ እያለሁ ፤ ተፈጠረ በተባለው ንቅናቄ ላይ ፤ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ከአስመራ ፤ አጠር ያለ ቃለ መጠይቅ አድርገው ፤ ሰፊ የሆኑ ጉዳዮችን ፤ ከላይ ከላይ ብቻ ገረፍ ገረፍ አድርገው ነው ያለፉት እያልኩ እያሰብኩ እያለሁ ፤ ቀጣዩዋ የአዲስ አመቷ ዋዜማ ምሽት ፤ ከሞላ አስገዶም ጆብዱ ጋር ሁሉንም ነገር እንክትክቱን አውጣችው ።

ያም ሆነ ይህ  ህዝብ የማወቅ መብት አለውና ፤ ጋዜጠኞችም የማሳወቅ ግዴታ አለብንና ፤ ወደ ሌሎች ጉዳዮች ከማለፌ በፊት ፤ የጋራ ንቅናቄው ውስጥ ተካተቱ ስለተባሉት ርድጅቶች ምንነት የማውቀውን እነሆ ።

1ኛ) ዴሞክራሲያዊ ምንቅስቃስ ህዝቢ ትግራይ ፤ ዴምህትን (TPDM) ድርጅታዊ ማንነት ከዚህ በፊት ራሱን በቻለ ፅሁፍ ብገልፀውም ፤ የአዲሱ አመት ዋዜማ ክስተት ፤ ከሞላ አስገዶም ተግባር ጋር ፤ የበለጠ እንደ ክሪስታል ጥርት ብሎ እንዲታየን ፤ መንገዱን ሁሉ ከፍቶልናል ፤ ስለዚህ ድርጅት በቂ ግንዛቤ ይኖራል ብዬ ስለገመትኩ በዚሁ ልተወው ።

2ኛ) አርበኞችና ግንቦት ሰባት እያንዳንዳቸው ሊኖራቸው የሚችለውን የሰው ሃይልም እንዲሁ ገልጬ ፅፌ ነበር ። ለማስታወስ ያህል ፤ በአጠቃላይ ከሁለቱ ድርጅቶች ከ150 ያልዘለለ የሰው ሃይል ሊኖራቸው እንደሚችልም ጠቁሜአለሁ ።፤ ከወደ አስመራም ፤ ይህ ውህደት በራሱ ችግር ላይ እንዳለ የሚያሳዩ ምልክቶች  ፤ እያየንም እየሰማን ነው ። የአርበኞች ግንባር ሰዎች ከግንቦት 7 ጋር በተደረገው ውህደት ደስተኞች እንዳልሆኑ ታውቋል ። ተራ አባላቱም ሆኑ የስራ አስፈጻሚ  ሰዎች ባገኙት አጋጣሚ እየኮበለሉ እንደሆነም እየታየ ነው ። እኔ ራሴ በሚገባ ላለፉት 10 አመታት ከአርበኞች ጋር የማውቀው ፤ የአርበኞች ግንባር መሪ የመአዛው ጌጡ የግል ሾፌርና የስራ አስፈፃሚ አባል ፈቃዱ ቸሬ በሱዳን በኩል አምልጦ ወደ ወያኔ ገብቷል ። በዚህ ላይ የአርበኞች ግንባር መሪዎች የነበሩ ሰዎች ፤ አንዳቸውም በየትኛውም ጥምረትም ሆነ ሌሎች አቢይ ክንውኖች ላይ ፤ ድምፃቸው እንደማይሰማ እያየንም እየሰማንም ነው ።

ከአስመራ በሚወጡ መረጃዎች  ፤ አርበኞች ግንባር ፤ ከግንቦት 7 ጋር ያለፈቃዳቸው ውህደት አድርጉ ተብለው በሻእቢያ ትእዛዝ እንደተሰጣቸው ሰምተናል ። ውጪ ካሉ ሰዎች ጋር ግንኙነት እያደረጋችሁ ፤ መረጃ ታስተላልፋላችሁ  ፤ ተብለውም የእጅ ስልካቸውን እንዲያስረክቡ ተደርገዋል ። ስለድርጅት በሚገባ የሚረዳና ፤ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶችን ግንኙነትን ታሪክ ጠንቅቆ የሚረዳ ሰው ፤ እነዚህን  ምልክቶች ሲያስተውል የአርበኞች ግንባርና የግንቦት 7 ንቅናቄ ውህደት ገና ረግረግና ፤ መሰረት ያልያዘ መሆኑን መረዳት አይሳነውም ። በውህደት የቆዩባቸው ያለፉት 6 ወራትም ፤ ሁለት ራሳቸውን ችለው ለቆዩ ድርጅቶች ፤ ፍፁም ውህደት አድርገዋል ብሎ ለመናገር ፤ በቂ ጊዜ አይደለም ። ስለዚህ "አርበኞች ግንቦት 7" በራሱ እንደ ውህደት ፤ እግሩ በፅናት ያልቆመ "ወፌ ቆመች" እየተባለለት ያለ ርድጅት ነው ።

3ኛ) መግለጫው እንደሚያሳየው የአፋሮቹ ድርጅቶች ፤ ወደጋራ ንቅናቄ የመጡት ፤ ራሳቸውን ችለው እንደ አንድ ድርጅት ሳይሆን ፤ እነሱም የተለያዩ የአፋር ድርጅቶች **ህብረት** (አዎ ህብረት የሚለው ቃል ይሰመርበት) ሆነው ነው ። የአፋር ድርጅቶች አሉ ይባላሉ እንጂ ፤ አንድም ቦታ ይህን ሰሩ ሲባል ታይቶም ተሰምቶም አይታውቅም ። ስለዚህ የአፋር ድርጅቶች አሉ እየተባለ የሚወራው ከአስመራ የኮምፒሽታቶ ጎዳና ባዶ ወሬነት በላይ አይዘልም ። አሉ ብለን ብንወስድ እንኳ ፤ አንድ ሳይሆኑ በህብረት ስለመጡ ፤ እነዚህ ድርጅቶች በራሳቸው የፀና አንድነት የሌላቸው ስለሆኑ ፤ እንዴት ተደርጎ ነው "ኢትዮጵያን አገር አድን" የሚባለው አዲስ ንቅናቄ ውስጥ ጉልህ አስተዋፅኦ ሊኖራቸው የሚችለው? ቦዶ ናቸው ።

4ኛ) የዚህ የአዲሱ "አገር አድን ንቅናቄ" አንዱ አባል ድርጅት ደግሞ "የአማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ" የተባለው ድርጅት ነው ። ይህ ድርጅት በሃሬናው ባላምባራስ ፤ በኮለኔል ፍፁም ይስሃቅ ኢንጂነርነት ተጠፍጥፎ የተሰራ ድርጅት ነው ።

ነገሩ የሆነው እንዲህ ነው ።

ወቅቱ ግንቦት ሰባት ፤ ወታደራዊ ኃይሉን ማደራጀት የጀመረበት የመጀመሪያዎቹ ወራቶች ላይ ነው ። ግንቦት 7 በስድስት ወራት ውስጥ መንግስት መገልበጥ እንደሚችል (ሰበር ዜና) ያወጀበት ወቅትም ነበር ። ሁላችንም እንደምናስታውሰው ከዚህ አዋጅ ከጥቂት ወራት በኋላ ፤ ከግንቦት ሰባት ጋር በመተባበር መንግስት ለመገልበጥ አሲራችኋል ተብለው ፤ እነ ጀነራል አሳምነው ፅጌ ኢትዮጵያ ውስጥ ይታሰራሉ ። (ይህ ክስተት በራሱ ኤርትራ ውስጥ ሰፊ ታሪክ አለው ። ሌላ ጊዜ የምመለስበት ጉዳይ ይሆናል ።) ከነአሳምነው ፅጌ መታሰር በኋላ ፤ 6ቱ ወራትም ቀናቸውን ቆጥረው ያለምንም ኮሽታ ያልፋሉ ። ይህ በግንቦት 7 ደጋፊዎች ላይ ፤ ከፍተኛ የሆነ መደናገርን ፈጠረ ፤ ተስፋውም ሟሸሸ ።

ግንቦት 7 ፤ ይህን አላስፈላጊ ሁኔታ መሸፋፈን ስለነበረበት ፤ ከአገር ውስጥ ፤ ከደቡብ አፍሪካና ከኬንያ ሰዎች ተመልምለው በአስቸኳይ ወደ ኤርትራ እንዲገቡ እቅድ አወጣ ። ወደ ኤርትራ ሲገቡ ምን ተስፋ ተሰጥቷቸው እንደነበር ፤ ተመልምለው ወደ ኤርትራ ከገቡት ሰዎች የሰማነውናቸው ሁኔታዎች አሉ ። እነዚህ ሰዎች ዛሬም በህይወት ስላሉ ምስክርነታቸውን መስጠት ይችላሉ ። ወደፊትም የምንሰማቸው ጉዳዮች እንደሚኖሩ ይታወቃል ። ሆኖም ግን በዚያው ሰሞን ሌላ "ሰበር ዜና" ታወጀልን ። የወያኔ ቤተ-መንግስት ጥበቃ ዋና አዝዥ የነበሩ ግለ-ሰብ የግቦት ሰባትን ተዋጊ ኃይል ተቀላቀሉ ። ይህ ግለሰብ ኮለኔል አለበል አማረ ይባላሉ ሲል እወጀው አስታወቀ ።

እንደተባለውም ኮለኔል አለበል አማረ ኤርትራ ገብተው ተገኙ ። መጀመሪያ ላይ ከአንዳርጋቸውና ከሌላ አንድ ሰው ጋር መስራት ይጀምራሉ ። በኮለኔል አለበል በኩል ወደ አንድ ሺህ ሰዎች ፤ በጎንደር በኩል ይመጣሉ ተብሎ ቃል ተገብቶም ነበር ። ሌሎች አምስት መቶ ሰዎች በአፋር በኩል አዘጋጅቻለሁ ያለ ሌላ ግለ-ሰብ ፤ እንዲሁ ከግንቦት ሰባት ለትራንስፖርትና ለተለያዩ ወጪዎች ገንዘብ ሲከፈለው ቆይቶ ፤ የመጨረሻው ሰአት ሲደርስ ፤ አንድም ሰው ሳያቀርብ እንደአስማተኛው ሁዲኒ ፤ እልም ብሎ ጠፋ ። ከደቡብ አፍሪካም የተወሰኑ ሰዎች ይመጣሉ ተብሎ ነበር ።

ከኬንያ ወደ ኤርትራ ለመግባት የተመለመሉት ሰዎች ደግሞ 10 ነበሩ ። እነዚህ 10 ሰዎች ከተመለመሉ በኋላ የወር ወጪያቸው በግንቦት 7 እየተከፈላቸው ለወራት ኬንያ ውስጥ በእንክብካቤ ተይዘው ቆይተዋል ። ሆኖም ግን የመጨረሻዋ ሰአት ደርሳ ፤ ወደኤርትራ ለመሄድ ቪዛ እንዲወስዱ ሲጠሩ ፤ ጥሪውን አክብረው የተገኙት ሁለት ሰዎች ብቻ ነበሩ ።

ከነዚህ ሁለት ሰዎች አንዱ ነው ፤ በአስመራና በሃሬና ከአንዳርጋቸው ጋር ቦክስ የገጠመው ። ወድ አንባቢዎቼ ይህን ግለሰብ በክፉ እንዳታዩት እጠይቃለሁ ። የራሱ ምክንያቶች ነበሩትና ፤ ሲያስፈልግ እመጣበታለሁ ። አንድ የማከብርለት ሁኔታ ግን አለ ። አንባቢዎቼም የአክብሮቴን ምክንያት ትጋሩኝ ዘንድ ላካፍላችሁ ። ይህ ወንድም በኬንያ ስደት ላይ የነበረ ሰው ነው ። በUNHCR የውጭ እድል አግኝቶ ፕሮሰስ ጀምሮ ነበር ። ይህን እድል ትቶ ነበር ወደ ትግል ሜዳ ለመግባት የወሰነው ። ፕሮሰስ ያልነበረቻው 8ቱ ደሞዝተኞች ግን ፤ ጉዟቸው የምር ሆኖ ከኤርትራ ኤምባሲ ቪዛ እንዲቀበሉ ሲጠሩ ፤ እምጥ ይግቡ ስምጥ ሳይታወቅ ፤ የውሃ ሽታ ሆነው በአየር ላይ በነው ጠፉ ። ሆኖም ግን ያን ሰሞን የተወሰኑ ሰዎች ከኢትዮጵያ በጎንደር በኩል ወደኤርትራ ገቡ ።

እነዚህ ሰዎች ከኢትዮጵያ እንደገቡ ፤ የሻእቢያው የሃሬና ተጠሪ ኮለኔል ፍፁም ፤ ኮለኔል አለበል አማረንና ሌላውን ሰው ጠርቶ ፤ ግንቦት ሰባቶች የሚታመኑ አይደሉም ። ከCIA ጋር እንደሚሰሩ የኤርትራ መንግስት ደርሶባቸዋል ። ከኛ ጋር የሚኖራቸው ቆይታ የኛ መንግስት ውሳኔ እስኪሰጥበት ድረስ ብቻ ነው ። ስለዚህ እናንተ ሁለታችሁ የአማራ ድርጅት አቋቁሙ ሲል ይመክራቸዋል ። ኮለኔል አለበል አማረ ፤ ይህን እቅድ ተቀብሎ ፤ ድርጅቱን በሻእቢያ ድጋፍ ያቋቁማል ። አብሮት እንዲያቋቁም የታጨው ሰው ፤ ይህን የሻእቢያ እቅድ ስለጠላው ብዙም ሳይቆይ ፤ ድምፁን አጥፍቶ ፤ ኤርትራን ለቆ ይወጣል ።

ግንቦት 7 ወጫቸውን ከፍሎ ፤ ለግንቦት 7 ጦር ተመልምለው መጡ ፤ ከተባሉት ሰዎች ውስጥ 7ቱን ፤ ኮለኔል አለበል አማረ ፤ ፈልቅቆ በማውጣትና ራሱን የአማራው ድርጅት መሪ በማድረግ ድርጅቱን ይመሰርታል ። የዚህ ድርጅት መሪ ኮለኔል አለበል አማረ ኤርትራን ለቆ ፤ ዛሬ ስዊድን ውስጥ በስደተኝነት ነዋሪ ነው ። ድርጅቱን አስወጥቼ ወደ አገር ቤት አስገብቸዋለሁ ሲል ማወጅ ከጀመረ ይኸው ድፍን ሁለት አመቱ ። ይህ የአዲሱ "አገር አድን የጋራ ንቅናቄ" አባል ድርጅት ፤ ከስሙ በስተቀር ይኼ ነው የሚባል መሪም ሆነ አባላት የሌለው ድርጅት ነው ። በሰው ህይልም ምንም የሌለው ባዶ ነው ። ሌላ ባዶ ።

ከነዚህ ባዶ ድርጅቶች፤ ተነቃንቆ ተነቃንቆ : ነው እንግዲህ ፤ አዲሱ "ኢትዮጵያን አድን የጋራ ንቅናቄ" ተቋቋመ ተብሎ (ሰበር ዜና) የሰማነው ። ዜናውን በሰማን በሁለተኛው ቀን ነው ደግሞ ፤ የንቅናቄው ም/ሊቀ-መንበርና የዴምሕት መሪ ሞላ አስገዶም ከ683 ወታደሮቹ ጋር የኤርትራን ድንበር ፤ ከውስጥ ወደ ውጪ በርቅሶ የወጣው ።

ሞላ አስገዶምን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት በሃሬና የዴምህት ካምፕ ውስጥ ነበር ። የተገናኘነው ወደ አርበኞች ግንባር ካምፕ ከመድረሳችን በፊት ፤ እዚያው ሃሬና ካለው የዴምህት ካምፕ ውስጥ ነው ። ሃሬና ውስጥ የዴምሕትና የአርበኞች ግንባር ካምፖች ርቀት በእግር ከአስር ደቂቃ በላይ አይወስድም ። ወደ አርበኞቹ ግንባር ሃሬን ካምፕ ስሄድ የመጀመሪያዬው ጉዞዬ ነበር ። በሰሜን ኢትዮጵያ በኩል የተሰማሩትን አርበኞች ለማየት የነበረኝ ፍላጎት ከፍተኛ ነበር ። ሃሬና ከመድረሳችን በፊት ጉልች የምትባለውን ትንሽ ከተማ እንዳለፍን መኪናዎቻችን እንዲቆሙ ተደርጎ ፤ ሜዳ ላይ ከአንድ ሰአት በላይ እንድንቆይ ተደረገ ። የቆምንበትን ምክንያት ጠየቅሁ ። አርበኞቹ እናንተን ለመቀበል እየተዘጋጁ ስለሆነ ፤ አንዳንድ ነገሮችን እስከሚያጠናቅቁ ትንሽ ለመጠበቅ ነው ፤የሚል መልስ ተሰጠኝ ።

የሆነው ግን ሌላ ነበር ። መጀመሪያ የተወሰድነው ወደ አርበኞች ግንባር ሳይሆን ፤ ወደ ዴምሕቶች ሃሬና ካምፕ ነበር ። እዚያ እንደደረስን ለኛ ብቻ ሳይሆን ፤ ከአስመራ ጀምሮ አብረውን ለተጓዙት ፤ የሻእቢያ ከፍተኛ የሲቪል ባለስልጣናት ፤ የሙዚቃ ባንድ አባላትና ፤ የሻእቢያ የጦር መኮንኖች ቁርስ ተዘጋጅቶ ጠበቀን ። ሞላን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት እንግዲህ እኛን እንግዶቹን ለመቀበል ሲደረግ በነበረው መስተንግዶ ፤ በዚህ የቁርስ ግብዣ ላይ ነው ። ያኔ ታዲያ ከመተዋወቅ በስተቀር ለጥቂት ጊዜ እንኳ ፤ ቁጭ ብለን ያወጋንበት አጋጣሚ ትዝ አይለኝም ። የያኔው የዴምሕት መሪ ሟቹ ፍስኃ ኀ/ማርያም ስለነበር ፤ ማናቸውም ንግግሮች ሁሉ የሚደረጉት በሱ በኩል ብቻ ነበርና ፤ሞላ አስገዶም አንፀባርቆ ሊታይ የሚችልበት አጋጣሚም አልነበረም ። ሆኖም ከፍስኃ ኀ/ማርያም ሞት በኋላ ፤ ካደረግኳቸው ተደጋጋሚ ጉዞዎቼ በአንዱ ላይ ከሞላ አስገዶም ጋር የመገናኘት እድል አጋጥሞኝ ነበር ።

በዋሽንግቶን ዲሲ አካባቢ በራዲዮ ፤ ለመላው አለም ደግሞ በኢንተርኔት ፤ አስተላልፈው የነበረውን የራዲዮ ፕሮግራሜ ፤ ወደ አስመራ በተደጋጋሚ አደርጋቸው ከነበሩ ጉዞዎቼ ጋር ፤ መጣጣም አልቻሉም ። ለኔ ያኔ ዋና ጥረቴ የነበረው ፤ የራዲዮ ቅስቀሳውን ስራ ወደ አገርቤት ማስገባት ነበር ።

እኔ አደርገው ከነበረው ጥረት በተሻለ ፤ በጊዜው የኤርትራ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ከነበሩት ከአቶ አሊ አብዶ ጋር ፤ አቶ ስለሺ ጥላሁንና ኢልያስ ክፍሌ ስምምነት ላይ ደረሱ ። ለአርበኞች ግንባር የራዲዮ ፕሮግራም እንዲጀመር ፈቃዱ እንዲገኝ አደረጉ ። ይህ በአርበኞች ግንባር አባላት ዘንድ ከፍተኛ ደስታን ፈጠረ ። ስለሆነም ለራዲዮ ዝግጅቱ ስራ ስቱዲዮ ያስፈልግ ነበር ። እዚህ በአሜሪካ ፤ በመኖሪያ ቤቴ ውስጥ የነበረውን የራዲዮ ስቱዲዮ ፤ ነቅዬ ወደ አስመራ አዛወርኩት ። ትንሽ ማስፋትም ያስፈልግ ስለነበር ፤ አቶ ስለሺ ጥላሁን ከለንደን የላከው ፤ ሌላ ተጨማሪ መሳሪያ ጋር በማዳመር ስቱዲዮውን ለአርበኞች ከፈትኩ ። ለፕሮግራም አዘጋጆቹም አስፈላጊውን የመጀመሪያ ደረጃ ስልጠና ሰጠሁ ። ከዚህ በኋላ ወደ ዋሽንግተን ኑሮየ መመለስ ነበረብኝ ።

እኔ ከተመለስኩ በኋላ ፤ ስለሺና ኤልያስ ከኢሳኢያስ ጋር ቀጠሮ ተይዞላቸዋል ። በዚህ ቀጠሮ ላይ የአርበኞች ግንባር አመራርም አብሮ ከነኤልያስና ከነስለሺ ጋር ፤ ወደ ቤተ-መንግስት እንዲገባ ተፈቅዶለት ነበር ። ከነኤልያስ ጋርም እስከቤተመንግስት ድረስ ሄዷል ። ኋላ ላይ ግን ፕሬዚደንቱ ለናንተ የያዙት ሰአት አልቋል በሚል ሰበብ ፤

የአርበኞቹ መሪዎች ፤ ኢሳኢያስን ሳያዩትና ሳያገኙት ተመልሰዋል ። ይህን ሁሉ እቅድ ፤ እነሞላ አስገዶም ሰምተውታል ። ዴምሕት ከማንም የተሻለ ዝግጅትና ወታደራዊ ሃይል እያለው ፤ እንደ አርበኞች ግንባር ፤ ፍላጎታቸውን የሚያሰማላቸው ፤ሰው ስለሌላቸው ፤ የመንፈስ ቅናት ሳያድርባቸው አልቀረም ። ስለዚህ በራሳቸው ጥያቄ ፤ ስለሺንና ኤልያስን ለማግኘት ፈልገዋል ። የምሳው ግንኙነትም በዚሁ ጉዳይ ላይ ያተኮረ ነበር ።

ይህች ቀን ደግሞ ለኔ የሄድኩበትን ጉዳይ ጨርሼ ፤ ምሽት ላይ ወደ ዋሽንግተን የምበርባት ቀን ነበረች ። ከሞላ አስገዶምና ከረዳቱ ጋር ፤ መገናኘት የነበረባቸው ደግሞ ስለሺ ጥላሁንና ፤ ኤልያስ ክፍሌ ነበሩ ። እኔም ሳልጋበዝ በቦታው ተገኝቻለሁ ። የአበሻ ግብዣ ነዋ ! ዴምሕቶች ከስለሺና ከኤልያስ ጋር ቀጥሮ እንዳላቸው ኮለኔል ፍፁም ሲረዳ ፤ እሱም እንደኔው ድንኳን ሰባሪ ሆኗል ። አንባቢዎች እንደምትገምቱት ፤ የሁለታችን አመጣጥ በግብ ፤ የተለያየ ነበር ። በምሳው ላይ ኮለሌል ፍፁም ዝም ብሎ የባጡን የቆጡን መዘበራረቅ አበዛ ። ምንም አይነት ፍሬ ያለው ንግግር እንዳይደረግ ፍላጎት እንደነበረው በግልፅ ይታይ ነበር ። ኮለኔሉ ቀልድና ቧልት ቢያበዛም ፤ ቀልዱም ሆነ ቧልቱ ለዛቢስ ነበር ። በመኻከል የስለሺ ስልክ አቃጨለና ስለሺ ስልኩን ይዞ ወደ ውጪ ወጣ አለ ። ቀጠለና የኮለኔል ፍፁምም ስልክ እንዲሁ አቃጭሎ እሱም እንዲሁ ወጣ ። እኔ እልያስ ክፍሌ ፤ ሞላ አስገዶምና ረዳቱ ጠረጴዛው ላይ ቀረን ። የሞላ ረዳት አጋጣሚውን በመጠቀም ኤልያስን እጁን ይዞት ወደ ጓሮ ወጣ አለ ።

እኔና ሞላ አስገዶም ብቻችንን ቀረን ። የምናወራው ነገር ስላልነበረ ፤ ወጋችን እንዲሁ ጉንጭ አልፋ የባጡን የቆጡን ወሬ ነበር ። በአጠቃላይ ሞላ አስገዶም ንግግር ለማሳመር የሚጥር ሰው አይደለም ። ብዙ ማውራትም ተፈጥሮው አይደለም ። ማዳመጥ ላይ ግን ንቁ ሰው ይመስላል ። ወታደራዊ ብቃቱንም በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ላይ ያስመሰከረ ጀግና ወታደር ነው ። በትእዛዝ ቁሙ እስከሚባሉ ድረስ ፤ በረዳት አዋጊ ደረጃ ባረንቱ ድረስ ዘልቆ የገባውን ጦር ከመሩት ሰዎች ውስጥ አንዱ ነው ። ወታደራዊ ችሎታውን ወዳጆቹም ሆኑ ጠላቶቹ በሚገባ ያውቁታል ።

ኤልያስና የሞላ አስገዶም ረዳት ፤ ኮለኔል ፍፁም ሳይጋበዝ እዚህ ምሳ ላይ የተገኘው ፤ ከነኤልያስ ጋር ሊደረግ የሚችለው ንግግር ላይ መሰናከል ለመሆን እንደሆነ ገብቷቸዋል ። በነኤልያስም በኩል ይኸው ግንዛቤ ተይዟል ። ስለዚህም ኤልያስና የሞላ ረዳት ጊዜ ሳያጠፉ ቶሎ ተመለሱ ። ባይነጋገሩም ሞላና ረዳቱ መልእክቱ በሚገባ በአጭሩ መድረሱ ላይ ተግባብተዋል ። እኔም የሆነ ነገር እንዳለ ስለተሰማኝ ፤ ምሳው አልቆ ጉዳዩን ልሰማ ጓጉቻለሁ ። ኋላ ላይ ከኤልያስ እንደተረዳሁት መልእክቱ ፤ “ መታገል እየፈለግን ያለ ምንም እንቅስቃሴ ፤ በየካንፑ ተወዝፈን ነውና የምንውለው ፤ በነፃነትና በምንፈልገው መንገድ ፤ እንዋጋ ዘንድ ኢሳኢያስ አፈወርቂን ጠይቁልን” የሚል ነበር ። ( አንድ ሌላ ተጨማሪ ጥያቄም ነበር ። ከዛሬው ፅሁፌ ጋር ምንም ግንኙነት ስለሌለው አስፈላጊነቱ አልታየኝም) ከዚህ የምሳ ግንኙነት በኋላ ኤልያስንና ስለሺን እዚያው አስመራ ትቻቸው ፤ የዛኑ ለት ማታ ፤ የተሳፈርኩበት አውሮፕላን ፀጥተኛውን የአስመራ ምሽት ሰንጥቆ ወደ ዋሽንግተን ይዞኝ እብስ አለ ።

ሞላ አስገዶም በ 1973 እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ገና በልጅነቱ ነው ወያኔን የተቀላቀለው ። ከዚያ የወጣትነት እድሜው ጀምሮ ህይወቱ በውትድርና ያለፈ ሰው ነው ። የውትድርና ችሎታ አንድም በተፈጥሮ አለያም በትምህርት የሚገኝ ነው ። ሞላ አስገዶም በተፈጥሮው ወታደር ነው ። ወታደራዊ ችሎታውንም ፤ ለምሳሌ ከላይ እንደገለፅኩት በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት ፤ በባሬንቱ በኩል የሻእቢያን ጀርባ ሰንጥቆ በመግባት አሳይቷል ።

ሞላ አስገዶም ፤ ባለፈው ሳምንት በኤርትራና ሱዳን ድንበር ላይ ፤ የፈፀመው ታሪክ ደግሞ ማንም ወደደም ጠላም አሌ የማይለው ወታደራዊ ችሎታውን ያሳዬበት ሁኔታ ነው ። አንድ ባታሊዮን ጦር ይዞ ፤ የኤርትራን ድንበር ከውስጥ ወደ ውጪ በርቅሶ መውጣት ፤ የወታደራዊ ስትራቴጂ ችሎታንና ብቃትን ያሳያል ። በምእራቡ አለም በስደት ላይ የምትኖሩ ፤ ህሊና ያላችሁ ፤ ኢትዮጵያውያን ወታደራዊ ጠበብቶች እንዳላችሁ አውቃለሁ ። በወታደራዊ ጥበብ አኳያ ይህን ድርጊት እንድትተቹበት በዚህ አጋጣሚ እጋብዛለሁ ።

እንዲህ እንደ ሞላ አይነት ወታደራዊ ተግባር ሲፈፀም ፤ ወታደራዊ ጠበብቶች ፤ “የጀነራሎች አርት(art)” በማለት ይጠሩታል ። ወታደሮችህን በሚገባ ማዘጋጀት ፤ የዘመቻ ፕላንህን በሚገባ መምራት ፤ የሃይልህን እንቅስቃሴና አሰፋፈር ጠንቅቆ ማወቅ ፤ በመጨርሻም የጠላትህን ትኩረት ወደ ሌላ አቅጣጫ ማዞር ፤ ከአንድ ወታደራዊ መሪ የሚጠበቅ ነው ። ሞላ አስገዶም ይህንን ሁሉ ፈፅሞ ፤ የሻእቢያን ድንበር አጥር ፤ እጅግ ውሱን የሆነ መስዋእትነት ብቻ ከፍሎ ፤ 683 ወታደሮቹን ይዞ ወደ ሱዳን ገብቷል ። ይህ ማንም የማይክደው ሃቅ ነው ። የፈቀደም ፤ ያልፈቀደም፤ ደስ ያለውም ፤ ደስ ያላለውም ፤ አይኑን አፍጥጦ አይቶታል ። ይህ ወታደራዊ ታሪክ በታሪካችን መዝገብ ውስጥ የራሱን ስፍራ ይዟል ። ሃውልቱን ተክሏል ። የዚህ ወታደራዊ ተግባር ፤ ኀውልት ባለቤት ደግሞ ፤ ከገበሬ ቤተሰብ የተወለደው የገበሬው ልጅ ፤ ሞላ አስገዶም ነው ። አበቃ ።

ከዚህ በኋላ የሞላ ድርጊት ያላስደሰታቸው ሰዎች በሹመት ድልድል አኩርፎ ነው ፡ በሙስና ተዘፍቆ ነው ፤ ከሃዲ ነው ፤ በማለት ስሙን የማጠልሸት ዘመቻ እየሞከሩበት ነው ። ያም ሆኖ ታዲያ እያበራ ያለን ኮከብ ላለማየት ፤ የራስን መዳፍ ፤ አይን ላይ መጋረድ ይቻል እንደሁ እንጂ ፤ ኮኮብን ተንጠራርቶ ማጥቆር ግን አይታለምም ።

ሞላ አስገዶም በምርጫው ላይ በሹመት አኩርፎ ነው ? በየትኛው ሹመት ? ሻእቢያ ዘንድ ሹመት የሚመጣው ከላይ በትእዛዝ ነው ። ሞላ አስገዶም ለ13 አመታት ይህን ያውቀዋል ። እንኳን ሞላ ቀርቶ ፤ እኔ ተመላላሹ ፤ ማን እንደሚሾም ትንቢት ተናግሬበት ተፈፅሞ አይተነው የለም እንዴ ?

በሙስና ነው ለተባለው አንድም ማስረጃ እስካሁን ድረስ የቀረበ የለም ። የግንቦት ሰባት ካዝና ደግሞ ከዴምሕት ካዝና ጋር ምንም ግንኙነት የለውም ። ከእነ ኮለኔል ፍጹም ተርፎ ፤ ሞላ አስገዶም ሊምቦጫረቅበት የሚችል ገንዘብ ለመሆኑ ከየት ይመጣል ?

ከሁሉ የሚደንቀው ሞላ አስገዶም ከዳ የሚለው አባባል ነው ። ሞላ ማንን ነው የከዳው ? "ግንቦት 7ን" ? "አገር አድን ንቅናቄውን ?" ወይስ ሻእቢያን ?

አዎ ሞላ አስገዶም ሻእቢያ ላይ ክህደት ፈፅሟል ። ለ13 አመታት ሻእቢያ ሞላ ላይ ፤ በተለይ ባለፉት ሰባት አመታት ፤ ተስፋ ጥሎበት ቆይቷል ። ሻእቢያ በአደባባይ ወጥቶ ሞላ ከዶኛል ሲል ግን አልሰማንም ። ይህን ክህደት እያራገቡልን ያሉት ደግሞ ፤ በጉዳዩ ላይ ምንም ጥልቅ የማያደርጋቸው ክህደቱ ያልተፈፀመባቸው ሰዎች ናቸው ። ለምን ? የሻእቢያ አፈ-ቀላጤውች ስለሆኑ ነው ወይስ ሌላ ?

ዛሬ ላይ ሞላ ከሃዲ ነው እያሉ ወሬ የሚያጮሁ ሰዎች የግንቦት 7 ሰዎች ናቸው ። የግንቦት 7 ሰዎች ፤ ከአንዳርጋቸው ጊዜ ጀምሮ ፤ በዴምሕት ላይ ለመፈናጠጥ ተስፋ አድርገው ነበር ። አንዳርጋቸው ከኢሳት ጋር ያደረጋቸውን የቴሌቪዥን ቃለ-መጠይቆች በሙሉ ወደኋላ ተመልሶ መመልከት ይቻላል ። ዴምሕት ጀርባ ላይ ለመፈናጠጥ ደግሞ ፤ አስፈንጣሪ (bouncer) ድርጅት ማግኘት የግድ ነበር ። በነመአዛው ጌጡ የምትመራው አርበኞች ግንባር ለዚህ ተስማሚ ነበረችና ዶ/ር ብርሃኑ በሌሉበት ሊቀ-መንበር ሆነው ተሾሙባት ። በተወካይ ( በነአምን ዘለቀ ) አማካይነት ውህደት ተደረገ ። ሁሉም ነገር በእቅዱ መሰረት የሚሄድ መሰለ ። የመጨረሻው ታሪካዊ ሁኔታ ላይ ለመገኘትና ፤ የታላቁ ታሪክ ባለቤት ለመሆን ዶ/ር ብርሃኑ ሁለት አጃቢዎቻቸውን ይዘው ወደ አስመራ አቀኑ ። "የኢትዮጵያን አገር አድን ንቅናቄም" ጳጉሜ 3 ቀን ተመሰረት ተባለ ። ( ሰበር ዜና )። ጳጉሜ አምስት ቀን በአዲሱ አመት መባቻ ላይ ፤ የንቅናቄው ምክትል ሊቀ መንበር ሞላ አስገዶም ፤ ለመፈናጠጫ የታሰበው የንቅናቄውን መሰረት ዴምሕትን ንዶ ፤ ከስራ አስፈጻሚው 37 አባላት ውስጥ 26ቱን ይዞ ዴምሕትን ጭንቅላቱን ሰይፎት ወጣ ።

በዚህ አይነት ፤ የተናደው ምኞትና ተስፋ ፤ የግንቦት 7 እንጂ የሞላ አስገዶም አልነበረም ። በዚህ ሁኔታ ፍርስርሱ የወጣው ፤ የሻእቢያ ድንቅ ፈጠራ "የአገር አድን ንቅናቄው" ብቻ አልነበረም ፤ የግንቦት 7 ተስፋም ጭምር እንጂ ። ይህ ከሆነ ክህደት እየተባለ የሚወራው ፤ ሞላ አስገዶም ግንቦት 7 ላይ ክህደት አልፈፀመም ። ተግባራቸውና የመረጡት መንገድ ነው የከዳቸው ። ሞላ አስገዶም ዴምሕትን በዘመን ፤ የላብና የደም መስዋእትነት ከፍሎበታል ። ለምንድነው ለእናንተ ፍላጎት የሚዋጋው ወይም የሚሞተው ?

አንዳንድ ታዛቢዎች እንዲያውም እንዲህ እያሉ ይተቻሉ ። "ያለፈ የፖለቲካ ታሪክ ስንመለከት ፤ ቀስተ-ደመና የምትባል አንዲት ትንሽ ድርጅት ተይዞ ቅንጅትን ለማፍረስ ተጠቀሙባት ። ወደ ውጪ እንደወጡ ቅንጅትን አፍርሰው ግንቦት 7ን ገነቡበት ። አርበኞች ግንባርን ፤ ከአርበኞቹ ሰረቁት ። ዴምሕትን ግን አልሆነላቸውም ።"

እንደሚታወቀው ሞላ አስገዶም ሃሬና ወታደራዊ ካምፕ ውስጥ የነበሩትን ተዋጊዎች ነው ይዞ የሄደው ። አሁን እየደረሱ ያሉ ዜናዎች እንደሚያመላክቱት ፤ ከተሰነይ ከተማ ወጣ ብሎ የሚገኘው የዴምሀቱ ካምፕ ፤ እንዳለ ተበትኗል ። በካምፑ ውስጥ የቀሩት አቅመ-ደካሞችና ህፃናት ልጆች የታቀፉ ሴቶች ብቻ ናቸው ። ወታደሮቹ ካምፑን ለቀው ከነመሳሪያቸው በተለያየ አቅጣጫ ወደ ሱዳንና ኢትዮጵያ ዘልቀው በመግባት ላይ ናቸው ። ከሶስት ቀናት በፊት ፤ ባለፈው ሃሙስ የሞላ አስገዶምን ፈለግ በመከተል የራሳቸውን ቡድን ፈጥረው ከካምፑ የተበተኑት ተቀላቅለዋቸው ፤ ከሻእቢያ ወታደሮች ጋር በድንበር አካባቢ ውጊያ እያደረጉ ናቸው ።

ባለፈው ወር ጓዛቸውን ጠቅልለው ገቡ ፤ ከተባሉት ሶስት የአሜሪካ ዘማች በረኸኞች ውስጥ ፤ አንዱ ትላንት ወደ አርብ ወደ አሜሪካ መግባት ነበረባቸው ። ከሞላ አስገዶም ጥሎ መሄድ ጋር በተያያዘ የሚጣራ ጉዳይ ስላለ ፤ ላልተወሰን ጊዜ ከአስመራ እንዳይወጡ ተደርጓል ።

እንደተለመደው አንድ ጉዳይ ልተንብይና የዛሬውን ፅሁፌን ላብቃ ። አሟረተ አትበሉኝ እንጂ ፤ በሻእቢያ ምክንያት ፤ በቅርቡ ከዚህ ከአሜሪካ በሄዱት ወገኖች ላይ ፤ ሊከሰት የሚችል አዲስ ሁኔታ ይኖራል ። በዚህ ላይ ከሻእቢያ ጋር የሚደረጉ ስምምነቶች ሁሉ ፤ ወርድና ስፋታቸው በሻእቢያ እየተለኩ ስለሚዘጋጁ ፤ የፈለጉትና ያሰቡት ስለማይሆን ፤ ከሚቀጥለው የኢትዮጵያ አዲስ አመት በፊት ፤ አስመራን ለቀው ወደየመጡበት ይመለሳሉ ።

ሲፕቴምበር 19/2015
ላስ ቬጋስ ኒቫዳ ።

ሞላ አስገዶምን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት በሃሬና የዴምህት ካምፕ ውስጥ ነበር ። የተገናኘነው ወደ አርበኞች ግንባር ካምፕ ከመድረሳችን በፊት ፤ እዚያው ሃሬና ካለው የዴምህት ካምፕ ውስጥ ነው ። ሃሬና ውስጥ የዴምሕትና የአርበኞች ግንባር ካምፖች ርቀት በእግር ከአስር ደቂቃ በላይ አይወስድም ። ወደ አርበኞቹ ግንባር ሃሬን ካምፕ ስሄድ የመጀመሪያዬው ጉዞዬ ነበር ። በሰሜን ኢትዮጵያ በኩል የተሰማሩትን አርበኞች ለማየት የነበረኝ ፍላጎት ከፍተኛ ነበር ። ከተሰነይ ስንነሳ በችኮላ ስለነበር ከትኩስ ከሻይ በስተቀር በአፌ የዞረ ነገር አልነበረም ። ሃሬና ከመድረሳችን በፊት ጉልች የምትባለውን ትንሽ ከተማ እንዳለፍን መኪናዎቻችን እንዲቆሙ ተደርጎ ፤ ሜዳ ላይ ከአንድ ሰአት በላይ እንድንቆይ ተደረገ ። የቆምንበትን ምክንያት ጠየቅሁ ። አርበኞቹ እናንተን ለመቀበል እየተዘጋጁ ስለሆነ ፤ አንዳንድ ነገሮችን እስከሚያጠናቅቁ ትንሽ ለመጠበቅ ነው ፤የሚል መልስ ተሰጠኝ ። የሆነው ግን ሌላ ነበር ። መጀመሪያ የተወሰድነው ወደ አርበኞች ሳይሆን ወደ ዴምሕቶች ሃሬና ካምፕ ነበር ። እዚያ እንደደረስን ለኛ ብቻ ሳይሆን ፤ ከአስመራ ጀምሮ አብረውን ለተጓዙት ፤ የሻእቢያ ሲቪል ከፍተኛ ባለስልጣናት ፤ የሙዚቃ ባንድ አባላትና ፤ የሻእቢያ የጦር መኮንኖች ቁርስ ተዘጋጅቶ ጠበቀን ። ሞላን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት እንግዲህ እኛን እንግዶቹን ለመቀበል ሲያደርግ በነበረው በዚህ የቁርስ ግብዣ ላይ ነው ።

Breaking news refers to events that are currently developing, or "breaking." Breaking news usually refers to events that are unexpected, such as a plane crash or building fire. Breaking news can also refer to news that occurs late in the day, close to a news outlet's usual deadline.

ዶጋሊ ኩፊት

ደርጅቶቹን